

‹‹የቤተ ክርስቲያን ብርሀን ቅዱስ ያሬድ››

ዳዊት ደስታ
dawitdesta126@gmail.com

- ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሐዲስ እንደሚሉት:- "ቅዱስ ያሬድ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከራስ ጸጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ : ሙሉ አካሏ ነው::"



ዳዊት ደስታ
- dawitdesta126@gmail.com



1. መግቢያ

ቅዱስ ያሬድ ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ ነገሯ ነው። ዜማዋ ነው በእርሱ ዜማ እናመሰግናለን፣ መምህሮ ነው ስብከቶቿን በዘመናት ከፋፍሎ አስተምሯል፣ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አስተማሪ ነው፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምግቧና ሕይወቷ፥ ክብሯና ሞገሷ ነው።

ይህ ቅዱስ አባትም ይዘከር ዘንድ በሚታሰብበት ሕይወቱን፣ ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብሩ የተጻፉ መጻሕፍትን፣ አስተዋጽዖ፣ ትምህርቱን፣ በማንሳት ለዚህ መርሐ ግብር በሚሆን መልኩ ለመወያያ ይረዳ ዘንድ የዶ/ር አምሳሉ እና የመጋቢ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ ጽሑፍ እንደ መነሻ ተጠቅሜ አቀርባለው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



- ቅዱስ ያሬድ የመጀመርያዋን ዜማ የዘመረባት ቦታ እንኳን እንደ ዋዛ በድንጋይ ታጥራ ምልክት እንኳን የላትም። ከያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት በቀር ሀገሪቱ በስሙ ምንም አልሰየመችለትም። ቅዱስ ያሬድ ግን በዓለም ላይ የመጀመርያው የዜማ ኖታ/ምልክት/ ባለቤት ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

የቀጠለ...



ፕሮፌሰር ጌታቸዉ ታይሌ ‹‹የቅዱስ ያሬድ ታሪክና የግእዝ ስነ ጽሁፍ›› በሚል ርእስ ባቀረቡት ጥናት ‹‹ቅዱስ ያሬድ የኢትዮጵያ ቤ/ክ ታሪክ ሰዉ ሆኖ ሳለ ሊቃዉንቱቻችን ትምህርቱን ዓመታት እያሳለፉ፣ መምህራን እያፈራረቁ፣ በቅናት በጥንካሬና በኩራት ሲማሩ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ያሬድ ማን እንደሆነ ለማወቅና እኛንም ለማሳወቅ የሚገባዉን ምርምር ሲያደርጉ አልታየም።›› በማለት ያለዉን ክፍተት ያሳያሉ። /1993፤3/።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

2. ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን እንዴት ትዘክራቸዋለች።

- በስማቸው ቤተክርስቲያን ይታነጽላቸዋል።
- ጽላት ይቀረጽላቸዋል።
- ሥዕል ይሣልላቸዋል።
- ገድላቸውና ተአምራቸው ይጻፍላቸዋል።
- የመታሰቢያቸው ዕለት በወር በዓመት ተወስኖ ይከበርላቸዋል።
- በዕለተ ዕረፍታቸውና ቃል ኪዳን በተቀበሉበት ዕለት ገድላቸው ተአምራታቸው ቃል ኪዳናቸው ይነገርላቸዋል። ማሕሌት ይቆምላቸዋል። በተለይ በስማቸው በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ቅዳሴ ይቀደሳል ዝክር ይዘከራል። በአጠቃላይ በዓላቸው በድምቀት ይከበራል። ቅዱስ ያሬድም እንዲህ ባለው ይታሰባል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

3. የሊቁ ዜና ሕይወት በጥቂቱ

- ቅዱስ ያሬድ የተወለደው በ505 ዓ/ም አክሱም አካባቢ ሲሆን እናቱ ክርስቲና (ታኡክልያ) አባቱ ደግሞ ይስሐቅ (አብድዩ) ይባላሉ።የትውልድ ሥፍራው አክሱም ነው።ምናኔ ደብረ ሐዊ ከተባለዉ ተራራ ላይ ብዙ ዓመታትን ካሳለፈ በኋላ በጸለምት ዋሻ በአንዱ ግንቦት 11 ቀን በ571 ዓ/ም ተሰወረ።

Born	**April 25, 505**
Died	May 20, 571 (aged 66)
Venerated in	Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Feast	11 Genbot

- **Saint Yared** (Ge'ez: ቅዱስ ያሬድ) (April 25, 505 – he Ethiopian Orthodox Church and Ethiopia's syster rly the chants of the Ethiopian Orthodox Tewahedo a feast day of 11 Genbot (May 19). His name is fro

4. ቅዱስ ያሬድ በቀሪ በሕይወቱ ዘመናት:-

1. መጻሕፍትን ጽፏል::

2. በጣና ቂርቆስ በዙር አባና በሌሎችም ቦታዎች ወንበር ዘርግቶ ብዙ ደቀመዛሙርትን አፍርቷል::

3. በሰሜን ተራሮች አካባቢ በተባሕትዎ ኑሯል::

በ576 (571) ዓ/ም በተወለደ በ71 ዓመቱ ግንቦት 11 ቀን ተሰውሯል::

4. ስብከተ ወንጌልን አስፋፍቷል። ታላቁ የኢትዮጵያ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ የክርስትና ሃይማኖት መሰረት ለሆኑት ዜማዎች፡ ዝማሬዎች፡ ወረብ፡ ሽብሸባ፡ ፈጣሪ አባት ነው። የቅዱስ ያሬድ ጥዑመ ዜማዎች ለሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች፣ ለዖም፣ ለህዘንና ለመሳሰሉት ወቅቶች የተደረሱና የተዘጋጁ ናቸው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



4. የአየር ንብረት መሰረት አድርጎ የደረሳቸው ድርሰቶች አሉ። ትምህርቶችን በዘመናት ከፋፍሎ ማስተማሩ።

5. መጻሕፍትን አስማምቷል። ድርሰቶቹ ከተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት በማጣቀስ የተደረሱ ናቸው።

6. የግእዝ ቋንቋ ባለ ውለታ ነው። ቋንቋው ተጠብቆ እንዲቆይ አድርጎል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



5. መጻሕፍቶቻችን ስለ ቅዱስ ያሬድ ምን ይላሉ?

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

- ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸውን መጻሕፍትና የጎላ ሊቃውንት ስለ እርሱ ክብር የጻፉትን በመጠኑ ይመለከታል። በሀገራችን ከሚገኙት መጻሕፍት ስለ ቅዱስ ያሬድ የሚናገሩ መጻሕፍት በርካታ ናቸው፤ በጥቅሉ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች እንመድባቸዋለን።

1ኛ. ራሱ ቅዱስ ያሬድ የጻፋቸው የዜማ መጻሕፍት ሲሆኑ፤

2ኛ. ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር የተደረሱ የምሥጋና ድርሰቶች፤

3ኛ የቅዱስ ያሬድን ታሪክ የያዙ ሌሎች መጻሕፍት ናቸው። ዝርዝራቸውን ቀጥሎ እንመልከት።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

5.1 እርሱ የጻፋቸው፤



- ቅዱስ ያሬድ የምሥጋና እና የአምልኮ መግለጫ የሆኑ የዜማ መጻሕፍትን በግዕዝ ቋንቋ ጽፏል። እነዚህም በስፋት የሚታወቁት አምስቱ የዜማ መጻሕፍቱና በታሪክና በትውፊት የተቀበልናቸው ሌሎች መጻሕፍት ናቸው። እነርሱም÷

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



1) ድጓ

- ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ውስጥ ትልቁ የዜማ መጽሐፍ ድጓ ሲሆን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለና በቤ/ክ ከዓመት እስከ ዓመት የሚደርስ ምስጋና ነው። በተለያዩ ዘመናት የተገለበጡ የድጓ ቅጂዎች በኢትዮጵያ የሚገኙ ሲሆን አንዳንድ ጠቃሚ እና ምትክ የማይገኝላቸው ቅጂዎች ከባሕር ማዶ ተሻግረው ይገኛሉ።

- (ለምሳሌ ቫቲካን [Vat.Aeth. 28]፣በርሊን [Orient. 1000])። በሀገራችን ከሚገኙት ዕድሜ-ጠገብ ድጓዎች መካከል በላሊበላ ቤተ-ጊዮርጊስ የሚገኘው(12ኛ መ/ክ/ዘ)፣ በጣና ቂርቆስ የሚገኘው (13 መ/ክ/ዘ)፣ በደብረ ብርሃን የሚገኘው (16ኛ መ/ክ/ዘ)፣ የሐይቁ ድጓ (17መ/ክ/ዘ)) ይጠቀሳሉ። “መጽሐተ፡ ጥቡብ” በመባል የሚታወቀው የቅድስት ቤተልሔም (ደ/ጎንደር) ድጓ ለምስክር አብነት ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



2) ጾመ ድጓ

- - በዐቢይ ጾም የሚደርስ ምሥጋና ነው። ጾመ ድጓ በዋናው ድጓ (ከአስተምህሮ ድጓ)ክፍል ተካቶ ይገኛል። ክፍሉ በዓቢይ ጾም ውስጥ ባሉት ሰንበታት ልክ ሲሆን ተራቸውም፤ ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኵራብ፣ መጻጕዕ፣ ደብረ፡ዘይት፣ ገብር፡ ሐር፣ ኒቆዲሞስ እና ሆሣዕና የሚል ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



3) ምዕራፍ -

- ይህ የዜማ መጽሐፍ ከመዝሙረ ዳዊት የተውጣጡ ምሥጋናዎችን በመስመር በመስመር እየከፈለ የሚደርስ የስብሐተ እግዚአብሔር መጽሐፍ ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



4) ዝማሬ-

- ማሕሌት ሲቆም የሚደርስ ሆኖ በጊዜ ቅዳሴ ከድርገት በኋላ የሚቀርብ ምሥጋና ነው። ዝማሬ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህም ጎብስት፣ ጽዋ፣ መንፈስ፣ አኮቴት እና ምስጢር የሚባሉት ናቸው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

5) መዋሥዕት -

- ካህናት በተዋሥኦ (በመቀባበል) የሚያዜሙት ሲሆን ክቡዐይ በጸሎተ ፍትሐት ጊዜ እና በቀዳም ሥዑር ዕለት የሚደርስ ምሥጋና ነው።

6) አንቀጸ ብርሃን -

- ቅዱስ ያሬድ ይህን የእመቤታችንን ምሥጋና የደረሰው በአክሱም ጽዮን ቤ/ክ ውስጥ ከታቦተ ጽዮን ፊት ቆሞ ነው። ገድሉ እና ተአምሩ (ሥስተኛው) እመቤታችንን እየለመነ አንቀጸ ብርሃንን በዕዝል ዜማ ሲያደርስ ቁመቱ አንድ ክንድ ያህል ከምድር ወደ ላይ ከፍ ይል እንደነበር መዝግበውታል። ለዚህ ጸሎት ምላሽ እመቤታችንም ተገልጻ በቃል ታናግረው ነበር።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



እርሱ የጻፋቸው፤

7) የሦስት ቅዱሳንን ገድል ጽፏል፤

- በትውፊት እንደሚታወቀው ቅዱስ ያሬድ ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል የሦስቱን ቅዱሳን ገድል ጽፏል። እነዚህም ገድለ አረጋዊ፣ ገድለ ጽሕማ እና ገድለ ይምአታ ናቸው።

8) ቅዳሴ -

- በቤተክርስቲያናችን የታተሙት ቅዳሴያት 14 በብዛት ይታወቃሉ፤ ነገር ግን ያልታተሙ ሌሎች ስድስት ቅዳሴያትም አሉ፤ የቅዱስ ያሬድ ቅዳሴም ካልታተሙት አንዱነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

5.2 ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር የተጻፉ

- ከኢትዮጵያ ቅዱሳን ሊቃውንት ግንባር ቀደም የሆነው ማሕሌታይ ያሬድ በዜማ ደራሲነቱ በዓለም ደረጃ የሚታወቅ ሲሆን ካበረከተው ዘመን ተሻጋሪ ሥራ አኳያ ስናየው ግን ስለእርሱ ክብር የተጻፈው አነስተኛ ነው። ድርሳን እና ገድል ተጽፎለታል ሆኖም በጣም አጫጭር ናቸው።
- እስካሁን ከተገኙት ውስጥ ዕድሜ ጠገብ የሆነው በሐይቅ ገዳም (ደቡብ ወሎ) ከሚገኘው “ገድለ ቅዱሳን” ውስጥ የሚገኘው “ድርሳን ወገድል ዘቅዱስ ያሬድ” ሲሆን የተጻፈበት (የተቀዳበት) ዘመኑም በ16ኛው መ/ክ/ዘ ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



የቀጠለ...

- በሁለተኛ ደረጃ ጥንታዊ የሚባለው የቅዱስ ያሬድ ድርሰን እና ገድል በ17ኛው መ/ክ/ዘ/ የተጻፈው እና በሀገረ እንግሊዝ የሚገኘው ሲሆን፤
- ሦስተኛው ደግሞ በዘመዶ ማርያም (ሰሜን ወሎ) የሚገኘው ሲሆን ዘመኑም በ18ኛው መ/ክ/ዘ ነው። በ19ኛው እና በ20ኛው መ/ክ/ዘ ሌሎች በርካታ ቅጂዎች በብዙ ቦታዎች ይገኛሉ። በውጭ ሀገር ከሚገኙት ቅጂዎች ውስጥ በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የሚገኘውን ገድል ኮንቲሮሲኒ የሚባል ምሁር ከግዕዝ ወደ ላቲን ተርጉሞ እ.ኤ.አ. በ1904 አሳትሞታል። ድርሳን፣ ገድል፣ ተአምር እንዲሁም መልክአ ያሬድን ይዟል። ቀጥለን በዝርዝር እንመልከታቸው፤

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



- ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር የተጻፉ

1) ድርሳነ ያሬድ -

- ለቅዱስ ያሬድ ታሪክ ዋና ምንጭ ሆኖ የሚጠቀሰውና ከገድሉ ይልቅ ስፋት ያለው ድርሳኑ ነው።

2) ገድለ ያሬድ -

- የቅዱስ ያሬድን የሕይወት ታሪኩንና ተጋድሎውን ዜና በአጭሩ የሚዘክር መጽሐፍ ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር የተጻፉ

3) ተአምረ ያሬድ -

- ካህኑ ያሬድ የፈጸማቸው ገቢረ ተአምራት በርካታ ቢሆኑም በገድሉ ላይ ተመዝግበው የምናገኛው ግን ሦስት ናቸው።

4) መልክአ ያሬድ -

- የኋላ ሊቃውንት ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር እንዲሆን “መልክእ” ደርሰውለታል። ... ይህ መልክእ በብዙ ቦታ የሚገኝ ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር የተጻፉ

- 5) የግንቦት ፲፩ ስንክሳር ንባብ -
- ስለ ቅዱስ ያሬድ ሕይወት ይዘረዝራል።
- (እንዲሁም የባጅ - እንግሊዝኛ ትርጉም 1928፣የኮሊ - የፈረንሳይኛ ትርጉም 1997፣ የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ሕትመት - የአማርኛ ትርጉም 1993 ዓ.ም.)

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

ስለ ቅዱስ ያሬድ ክብር የተጻፉ

6) ነግሥ ዘያሬድ -

- ለቅዱስ ያሬድ ከተደረሱት የ“ነግሥ” ምሥጋናዎች መካከል አንዱ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የደረሰው ብሎ ይጀምራል ÷.....” ሁለተኛው ደግሞ አፄ ዘርአያዕቆብ የደረሰው ምሥጋና ነው።

7) አርኬ -

- ፓሪስ የሚገኘው (ኮንቲሮሲኒ ያሳተመው) እና በትንሣኤ ማሳተሚያ የታተመው የስንክሳሩ አርኬ ስለ ቅዱስ ያሬድ ምሥጋናውን ይናገራል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



5.3 ስለ ቅዱስ ያሬድ የሚያስረዱ ሌሎች መጻሕፍት

ዳዊት ደስታ
dawitdesta126@gmail.com

1) ገድለ አረጋዊ -



- ከላይ እንዳየነው በትውፊት የገድለ አቡነ አረጋዊ ጸሐፊ ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ ይነገራል። የታተመው ገድለ አረጋዊ የጸሐፊነቱን ሚና ለሌላ ይሰጠዋል፤ ሁለቱን ሃሣቦች ስናገናዝባቸው ሊሆን የሚችለው መጀመሪያ ያሬድ ጽፎት በኋላ ሌሎች ገልብጠውታል ማለት ነው።
- ወደ ገድለ አረጋዊ ስንዘልቅ በርካታ ቦታዎች ላይ የቅዱስ ያሬድን ታሪክ መዝግቦት ይገኛል። ያሬድ በዘመነ ገብረመስቀል ማሕሌቱን እንደ ጀመረ፣ ድርሰቱን ከብሉይ ከሐዲስ እንዳውጣጣው፣ ዜማውን ከመላእክት እንደሰማው፣ወዘተ.... ይዘረዝራል። እንዲሁም ወደ ደብረ ዳሞ ወጥቶ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲመለከት እንደነበር ይናገራል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

2) ድርሳነ ዑራኤል -

- የቅዱስ ያሬድን ታሪክ ከያዙት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መካከል አንዱ ድርሳነ ዑራኤል ሲሆን እመቤታችን ተገልጻ ቅዱስ ኤፍሬምንና አባ ሕርያቆስን “ዜማ እንዲደርስልኝ ውዳሴዬንና ቅዳሴዬን ለያሬድ ስጡት” ብላ እንዳዘዘቻቸውና ቅዱስ ያሬድም በተሰጠው ሀብተ ዜማ እንደ ዘመረ ይናገራል። ለቅዱስ ያሬድ ጽዋዓ ልቡና ያጠጣው መራሔ ብርሃናት ዑራኤል እንደሆነ ድርሳነ ዑራኤል ይገልጻል።
- ‹‹በመላእክት ምስጋና ሦስት ዓመት አስተማረባት›› በማለት በዙር አባ ማስተማሩን ይገልጻል።/ድርሳነ ዑራኤል/

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

3) መጽሐፈ አክሱም -

- ይህ መጽሐፍ የአክሱም ጽዮንን ታሪክ እና የርስት ጉልቷን ሥሪት የሚናገር ሲሆን ስለ ቅዱስ ያሬድ ዜማ ድርሰት ይናገራል። እንዲሁም ከላይ በድርሳነ ዑራኤል የተገለጸውን ታሪክ (እመቤታችን ተገልጻ ቅዱስ ኤፍሬምንና አባ ሕርያቆስን "ዜማ እንዲደርስልኝ ውዳሴዬንና ቅዳሴዬን ለያሬድ ስጡት" ያለችውን) መዝግቧል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

4) ታሪክ ነግሥት -



- የኢትዮጵያን ታሪክ ከያዙት መጻሕፍት አንዱ የሆነው የዙር አባ (ዙራምባ) ታሪክ ነግሥት የቅዱስ ያሬድን ታሪክ የያዘ ሲሆን በተለይ በዑራኤል መሪነት ከአጼ ገ/መስቀልና አባ አረጋዊ ጋር ወደ ዙርአባ ተራራ እንደወጡ፣ በዙር አባ ለሦስት ዓመታት ቅዱስ ያሬድ ዝማሬና መዋሥዕትን እንዳስተማረ ይናገራል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

5. ቅዳሴ ማርያም



- በትርጓሜ ቅዳሴ ማርያም መቅድም ላይ እንደምናነብበው ቅዱስ ያሬድ ማይኪራህ በተባለው ቦታ ተሰውሮ ጸዋትወ ዜማን ሲያስተምር እመቤታችን ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬምን የብህንሳውን አባ ሕርያቆስን በአካለ ነፍስ እንዲመጡ አድርጋ ኤፍሬም ውዳሴዬን፤ ሕርያቆስ ቅዳሴዬን ነግራችኹት ቅዱስ ያሬድ በዜማ ይድረስልኝ ብላ ነግረውት በዜማ ደርሶታል፤ ይኽም ሊታወቅ ሥረይ በቅዳሴ ማርያም ይበዛል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

6. ተአምኖ ቅዱሳን ንባቡና ትርጓሜው

- ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በተአምኖ ቅዱሳን መጽሐፉ ላይ ማኅቶተ ቤተክርስቲያን ሊቁ ቅዱስ ያሬድን ሲያወድስ፡-‹‹የመንፈስ ቅዱስን ምግብን የጠገበ፤ ከመጻሕፍት ሹሉ ትርጓሜያተ ድርሰትን ያሰባሰበ፤ ሃሌሉያ በሚል ምስጋና የኢትዮጵያ ሀገርን በጥዑም ማሕሌትና በሚያምር ምስጋና ያስጌጠ፤ የመለኮት ቃልን በላይዋ ላይ እንደንጹሕ የወርቅ ሻሻቴ ያፈሰሰ ለሹነ ለካህኑ ያሬድ ሰላምታ ይገባል›› ይለዋል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

6. የቅዱስ ያሬድ አስተዋጽኦ

ቅዱስ ያሬድ ለቤተ ክርስቲያን ለሀገርም ያደረገዉ አስተዋጽኦ ተዘርዝሮ አያልቅም። በቤተ ክርስቲያንበ እያንዳንዱ አገልግሎት የሚወሳ ነዉ።

- ሰማያዊ ዜማን ከማበርከቱም ሌላ
- በትምህርት ሂደትም አስተዋጽዖ አድርጓል። የድጓን፣ የጾመ ድጓን የዝማሬ መዋሥዕትንና የቅዳሴን ትምህርት ከማስተማሩም በላይ ለቅኔ ትምህርትም መሠረት ጥሏል።
- በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያናችን አምድ፣ የውስጥ ማኅቶት፣ የአፍ መብራት፣ በጠቅላላዉ የቤተ ክርስቲያን መንቀሳቀሻ ሕይወት ነዉ።
-

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

1. ሥርዓትን ሠርቷል

- የቅዱስ ያሬድ ሥርዓተ ማኅሌት ከአለባበስ ጀምሮ ሕግና ሥርዓት አለው፤ ቅዱስ ያሬድ ፡-ንጹሕ ልብስ ተጐናጽፎ፥ ነጭ ሻሽ አምሮና ጠምጥሞ የመላእክትን አክሊል አስመስሎ፥ ጣዕመ ማኅሌቱን በከበሮ፣ በጸናጽልና በመቋሚያ ያቀርብ ነበር።
- ልጆቹና ተከታዮቹ የሆኑ ሊቃውንትም፡- የአባታቸውን የቅዱስ ያሬድን ሥርዓት ሳይለውጡ፥ የእርሱን ፈለግ ተከትለው ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ። ይህም፡- በቤተ ክርስቲያን ተወድዶ፣ ተከብሮና ጸንቶ የሚኖር የቅድስና ሥርዓት ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

- ሊቁ የኔታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ፡- “ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌተ ዝአቡነ ያሬድ፤” በሚለው መጽሐፋቸው፡-
- “ንዋያተ ማኅሌት ከጥንት ከነ ሙሴ ጀምሮ ከሌዋውያን ካህናትና ከነቢያት የመጡ የተወረሱ፥ መሠረታዊ ባህልና ሥርዓት ሆነው ለስብሐተ እግዚአብሔር ናቸው እንጂ ለዘፈን አይደሉም። . . . እኛም አባታችንና መምህራችን ቅዱስ ያሬድ የሠራልንንና ያስተማረንን የዜማ ምስጋና በንጽሐ ጠባይዕ ሁነን፥ በጸናጽልና በከበሮ ለእግዚአብሔር ስንዘምር ጠላታችንን ዲያብሎስን ከጭፍሮቹ አጋንንት ጋር ድል አድርገን፥ ባሕረ ኃጢአትን ተሻግረን፥ ርስተ መንግሥተ ሰማያትን እንወርስበታለን።...ስለዚህ ማኅሌተ ቅዱስ ያሬድ ከቅዱሳት መጻሕፍት ተገኝቶ የተነገረ ነው እንጂ ሥረ መሠረት እንደሌለው ነገር የሚናቅና የሚወድቅ አይደለም፤” ብለዋል።/ዘፀ፡፲፭÷፩-፳፩፣ኢያ፡፭÷፮ ፲፮፣ መዝ፡፻፶።/
- (ጥ/ሥ/ማ ዘአቡነ ያሬድ ገጽ ፩፭፱-፪፻፩)

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

የቀጠለ...



- ቅዱስ ያሬድ በሰዓታት በወራት እና በዘመናት የተከፋፈሉ ድንቅ ምሥጢር የያዙ መዝሙራትን (ምስጋና) ከብሉያትና ከሐዲሳት ለቤተክርስቲያን እንደ ንብ ቀስሞ እንደ ሰምና ወርቅ አስማምቶ የአገልግሎት ሥርዓትን የሠራ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

2. የመጀመሪያው ደራሲ ነው።

የቅዱስ ያሬድ አስተዋጽኦ እና በብዙዎች ዘንድ የማይታወቀው ሥራው በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው ደራሲ እሱ መሆኑ ነው። እስካሁን በተደረገው ጥናት የኢትዮጵያ ጽሑፎች እስከ ያሬድ መነሳት ድረስ ትርጉሞች (በተለይ ከግሪክ ቋንቋ) ነበሩ። ብሔራዊ ድርሰትን (ሀገር በቀል) በኢትዮጵያ የጀመረ ቅዱስ ያሬድ ነው።

ቅዱስ ያሬድ የተነሳዉ ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ዘመን ነዉ። በዘጠኙ ቅዱሳን የተተረጎሙት ቅዱሳን መጻሕፍት በቅዱስ ያሬድ የድርሰት ስራ ዉስጥ ጉልህ ድርሻ ነበራቸዉ። ቅዱስ ያሬድ ከመጻሕፍቱ ያገኛቸዉን ምስጢራት ቃል በቃል እየጠቀሰ እንዲሁም ሐሳባቸዉን ጨምቆ በመዉሰድ በራሱ ቋንቋ እያራቀቀ ለድርሰቱ ተጠቅሞባቸዋል።

/ሰሎሞን ወንድሙ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ሕይወት፤1998 ገጽ15/።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

3. ስብከተ ወንጌል በማዳረስ

- ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያና በተለያዩ ቦታዎች ዞሮ በማስተማሩ፣ ከእግዚአብሔር ተልኮ ሰማያዊውን የመላእክት ዜማ በማስተማሩ፣ የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ የእመቤታችንን ክብር ከመመስከሩ በተጨማሪ የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፣ የጻድቃንን፣ የሰማዕታትን፣ የመላእክትን ክብራቸውን በመግለጽ መስክሯልና ምስክር ይባላል። ቅዱስ ያሬድ በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር የተለያዩ ሐዋርያዊ አገልግሎችን አከናውኗል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com




4. የግእዝ ቋንቋ ባለ ውለታ ነው።

የደረሳቸው ድርሰቶች በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ስለሆነ ተጠብቆ እንዲቆይ አድርጎል።

አባቶቻችን:-

- *ጥዑመ ልሳን
  *ንሕብ
  *ሊቀ ሊቃውንት
  *የሱራፌል አምሳያ
  *የቤተክርስቲያን እንዚራ
  *ካህነ ስብሐት
  *መዘምር ዘበድርሳን
  *ማኅሌታይ
  *ልዑለ ስብከት



- የዜማ አባት÷ ቀማሪና አቀናባሪ፣ የቅኔ ፈላስፋ፣ የመጻሕፍት ደራሲ፣ የብሉያት ሊቅ፣ የሐዲሳት መምህር፣ ካህኑ ለእግዚአብሔር፣ ጻድቅ ሰው፣ መናኝ ገዳማዊ፣ ማሕሌታይ፣ የቤተክርስቲያን ብርሃኗ፣ የሥርዓተ አምልኮ ልሳኗ፣ እያሉ ይጠሩታል::

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com

የሚነሱ ጥያቄዎች

1. ላይና በመጽሐፉ ስንክሳር እንደመዘገቡልን ግንቦት ፲፭ ቀን ቅዱስ ያሬድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በግድለ ቅዱስ ያሬድ ከዚህ ዓለም ውጣ ውረድ ያረፈበት ቀን ነው፤ እዚህ ላይ ግን አከራካሪ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም

1ኛው ቅዱስ ያሬድ ሞቶ ተቀብሯል የሚል ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ቅዱስ ያሬድ እስከነ ነፍሱ ተሠወረ እንጂ አልሞተም የሚል ነው። ቅዱስ ያሬድ ሞተ የሚሉ ወገኖች ከሚጠቅሷቸው ማስረጃዎች ውስጥ በመጽሐፉ ስንክሳር፡- ‹‹በዚህች ዕለት ማኅሌታይ ያሬድ ዐረፈ፤›› እና ‹‹ከዚህ በኋላ በሰላም ዐረፈ›› የሚሉት ሐረጋት የሚገኙ ሲሆን፣ ተሠወረ የሚሉት ደግሞ እዚያው ስንክሳሩ ላይ፡- ‹‹ከዚህ በኋላ ወደ ሰሜን አገር ሒዶ ግድሉን በዚያ ፈጸመ›› ተብሎ የተገለጸውን እንደማስረጃ ይጠቅሳሉ።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



ምላሽ

- ቃሉን በትኩረት ለተመለከው ሰው ዐረፈ ማለት ሞትን ብቻ ሳይሆን እንደነ ሄኖክ ከዚህ ዓለም ጣጣና እንግልት ተለይቶ በሕይወት እያሉ (ሳይሞቱ) ተሠውሮ መኖርንም ያመለክታል።
- ግድሉን በሰሜን አገር ፈጸመ የሚለውም መሠወሩን ብቻ ሳይሆን መሞቱንም ሊያመለክት ይችላል የሚሉም አሉ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መምህራን እንደሚያስተምሩን እነእግሌ ቀበሩት የሚል ቃል ስለማይገኝ ቅዱስ ያሬድ ተሠወረ እንጂ ሞተ ተብሎ አይነገርለትም። ለዚህም ማስረጃ እርሱ በተሠወረበት ተራራ እስከ አሁን ድረስ የከበሮ (የማኅሌት) ድምፅ ይሰማል፤ የዕጣን መዓዛ ይሸታል። ይህም ቅዱሱ ከሰው ዓይን ተሠውሮ እግዚአብሔርን እያመሰገነ እንደሚገኝ አመላካች ነው።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com



- 2. ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ያዘጋጀበት ዘመን ከ540-560 ዓ.ም. ባለው ጊዜ መሆኑ ይነገራል። ዜማውን ካዘጋጀ በኋላ 11 ዓመት አስተምሯል። በእርሱ ዘመን ተሰዓቱ ቅዱሳን በሃይማኖት ችግር ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጥተው ስለ ነበር ቅዱስ ያሬድ ከአንዱ ከአባ ጸንጠሌዎን የውጭውን ሀገር ቤተ ክርስቲያን ባሕልና ሥርዓት ይጠይቅ ነበር። በጅሮ የሰማውንም በዓይን ለማየት ሁለት ጊዜ ሮም የተባለችውን የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ጐበኘሁ ይላል። «ሮሜ ቤተ ክርስቲያን ሳበኝ፣ ሄድኩ» እንዲል።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com
•2008 ዓ.ም



- የታሪክ ምሁሩ ሥርግው ሀብለ ሥላሴ ለቁስጥንጥንያ ዜማ መነሻው ቅዱስ ያሬድ ነው ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ የሚያደርጉት የቁስጥንጥንያን ዜማ የደረሰው ሊቅ ዜማውን አገኘው የሚባለው የቅድስት ሶፍያን ቤተ ክርስቲያን ሲዞር ከሰማው ዜማ ነው። ይህ ዘመን ደግሞ ቅዱስ ያሬድ ከተነሣበትና ወደ ሮሜ ሄድኩ ካለበት ዘመን ጋር ተመሳሳይ ነው። እናም ምናልባት ያ ሰው ዜማውን የሰማው የቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያንን እየዞረ ሲዘምር ከነበረው ከቅዱስ ያሬድ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። Ancient and medival Ethiopian History

ማጠቃለያ



- የቅዱስ ያሬድ ዜማ የመጠቁ፣ የምንኮራባቸዉ፣ የእኛን ማንነት ሊገልጹ የሚችሉ እና በድርሰቶቹ ዉስጥ ያሉት መልዕክቶች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ፣ ከመጥፎ ነገር እንድንቆጠብ፣ በጎ ነገርን እንድንይዝ፣ ጥበብን እንድንፈልግ፣ ሰላም እንዲኖረን የሚያስተምሩ ናቸዉ።›› ድርሰቶቹ ከመንፈሳዊዉ አስተምህሯቸዉ በተጨማሪ ሌሎች ሁኔታችን በማንሳት የሚያብራሩ ናቸዉ።
- ቤተ ክርስቲያን ለቅዱስ ያሬድ ጽኑና ታላቅ ፍቅር የተነሣ ንጽሕናዉን ‹ቅድስናዉንና መንፈሳዊ አገልግሎቱን አይታ በስሙ ጽላት ቀርጻ፣ ቤተ ክርስቲያን አንጻ፣ ገድል ጽፋ፣ ስታከብረዉና ስታመሰግነዉ ትኖራለች።

ዳዊት ደስታ
•dawitdesta126@gmail.com
•2008 ዓ.ም



አመሰግናለው